# ታሪክን የረሳ ስህተቱን ይደግማል

ብዙ ሰዎች ያለፈውን ማስታወስ ቂምና ቁርሾን ማጠናከር ይመስላቸዋል። አይደለም። ያለፈውን የምናስታውሰው ስህተትን ላለመድገም ነው -- ዳግም ጉዳት እንዳይደርስብን። ሲባል የፈሰሰ ደምንም ማስታወስና መዘከር፤ ፍትሕን መሻት አስፈላጊ አይደለም ከሚል አይደለም። ታሪክ በተለይም ደም የፈሰሰለት ከሆነ-- ቅርስና ትምህርትን ሰጪና አስተማሪ ነው። ዛሬ ስህተታችንን ስንደግምና ለጨቋኞች ሁሉ ሰለባ ሆነን ስንገኝ ታሪክን አንርሳ ማለት የግድ ይሆንብናል።

በቂ ተመክሮና ታሪክ ያለን ሕዝብ ሆነን ሳለ የዝቅተኛነት ስሜት እያየለብን የራሳችንን ታሪክ ማወቅ መገንዘብና በዚያም ተመክሮን ገምግሞ ትምህርት ከመቅሰም ይልቅ የባዕዳንን ታሪክ ማነብነቡን የመረጡ ጥቂቶች አይደሉም። ስንቶች ለራሳችን ተመክሮ ንቀት ስላላቸውም ሳያውቁት ያወቁትና ያጠናቀቁት ይመስላቸውና ሀ ብለው ፖለቲካ ትላንት ይጀምሩና ስንት ዓመት ሲታገሉ የነበሩትንና ስንት ተመክሮ ያካበቱትን ሊተቹ ይነሳሉ። ፈረንጅ አምላኪዎችና ለምዕራቡ ስልጣኔ ተንበርካኪ ሆነው የራሳቸውን ባህልና ቅርስ የሚያንቋሽሹ ማለት ነው። ታሪክ ሲረሳ ደግሞ ተኪው ትውልድ አቅጣጫ ይስትና ለጎጂ ባህሎችና ለሀሰት መረጃዎች ተገዢ ይሆናል---ሀገርም ትጎዳለች። ወያኔ ዘረኛና ገንጣይ ፖለቲካውን ያራመደው የኢትዮጵያን ታሪክ በመካድና የአንድነት ሀይሎችን በማጥቃት ነው። ወጣቶች--በትግራይ በቅድሚያ-- የታሪክ እውቀት መሰረት አጡና ወያኔ ላካሄደው ጸረ ኢትዮጵያና ጸረ አማራ ሰበካ ጆሮ ሰጡት። ሌላና ሀቀኛ ታሪክና አማራጭ እንዳይቀርብም ወያኔ የኢትዮጵያ ሀይሎችን ወግቶ ከትግራይ መሬት በሻዕቢያ ዕርዳታ ሊያርቅም ቻለ፡፡ ላለፉት 22 ዓመታት ወያኔ ታሪክን አስመልክቶ የነዛው ሀሰትና ከቅርብ ጊዜ ወዲህም በኢሕአፓ ላይ የከፈተው የሀሰት ታሪክ ዘመቻ የሚጠቀሱ ናቸው። ለህዝብ የተጋደለውን ጸረ ህዝብ፤ ኢትዮጵያ ያለውን ትምክህተኛ ፤ በሽብር የተጠቃውን ሽብርተኛ፤ መላ ህዝብን ደግሞ ጸረ ትግሬ ጠላት ብሎ ወያኔ የሚያቀርበው እውነቱ ከታወቀ ግቡ ስለማይሟለለት ነው። የኢትዮጵያ ታሪክ መቶ ዓመት አይሞላውም፤ ኤርትራ ቅኝ ግዛት ነበረች ለኢትዮጵያ፤ ኦሮሞው ሕዝብ ኢትዮጵያዊ አይደለም፤ ወዘተ ወዘተ በሚል ሳይታክት ወያኔ የሚለፍፈው ታሪክን ለማስረሳትና ለማስካድ ነው። በኢሕአፓ ላይ የተጧጧፈው ዘመቻም ይህን ድርጅት ከአዲሱ ትውልድ ለመነጠል ነው። ወያኔ በለስ ቀናውና ታዲያ የተሻለ ማወቅ የሚገባቸውም ታሪክን ማስታወስ ማወቅ እየተሳናቸው ለወያኔ ሀሰት ሰለባ ሆነዋል። ታሪክን ማወቅ ተስኗቸዋል፤ ያውቁ የነበሩትም ረስተውታል።

ወደ ኋላ መለስ ብለን ታሪካችንን ስንቃኝ የእርስ በርስ ክፍፍል ለጠላቶች እንዳመቸ እንገነዘባለን። ለሀገር አንድነትም እንቅፋት ሆኖ ባጅቷል። ወያኔ የፈረደባቸውን አጼ ምኒሊክን ኤርትራን አስወሰዱ ብሎ ሊከስ ቢከጅልም ይህ የሁሉ ስርአቶች ድክመት በተለይም አጼ ዮሓንስን የሚመለከት መሆኑን መቀበል ዘረኝነቱ አልፈቅድ ብሎታል። ወያኔ ኤርትራን አስገንጥሎ ሌሎችን ግን በዚሁ ክህደት ሊከስ ይሞክራል። ወያኔ ከወራሪው የዚያድ ባሬ የሶማሊያ ጦር ጎን ቆሞ ሳለ ሀቁን ሸምጥጦ ክዶ ሌሎችን ይከሳል-- ይህንንም የሚያስተጋቡለት ውድቆችንም አግኝቷል። ታሪክ ባዕዳን ለኢትዮጵያ ደግ እንዳልተመኙ፤ እንግሊዝ ልትወርና ልትገዛን ስንቴ እንደጣረች፤ ሙሶሊኒ ሲወረን ድጋፍ ከምዕራቦቹ እንዳገኘ፤ አሜሪካ በሁሉም የታሪክ አጋጣሚ ከሕዝብ ጠላት አገዛዞች ጋር እንደቆመችና የሕዝብንም የለውጥ ትግል እንዳደናቀፈች፤ ወዘተ እያስተማረን እምቢኝ ብለው ግን ዛሬም ባዕዳንን ማመንና አሜሪካ ነጻ ያወጣናል ብሎ መመኘትና ተስፋ ማድረጉ ተብትቦ የያዛቸው ጥቂት አይደሉም። ለአሜሪካ አድረውና ተቀጣሪ ሆነው ወያኔንም ሲያስወግዱ የሚታያቸው አሉ። ከዚህ ሌላ ከቶም ታሪክን ያለመገንዘብ ምን ስህተት አለ? ስንት መቶ ሺ ሕብን የፈጀውን አረመኔና ግብረ አበሮቹንስ የተበላሸና የተወገዘ ታሪክ ለማደስ የሚፍጨረጨት

ምን ሊባሉ ይችላሉ የወንጀል ተባባሪና የሀገርን ታሪክ ረጋጭ ከመባል ሌላ? ሀይሌ ሀይሌ ያሉት መንጌ መንጌ ሲሉና በዚሁ መንፈስ ሲቀጥሉ ታሪክን ረስተው፤ ተመክሮአችንን ረግጠው የሚሳለቁብን ናቸው።

ታሪክን መርሳት የሌለብን ሀገር አጥፊውን ሀገር ወዳድ ብለን አቅፈን ቀንበሩን በላያችን ላይ ጭነን ሀገራችንን ለውድቀት እንዳናጋልጥም ነው። ባለፈው የሰራናችውን ስህተቶች፤ የተደናገርንባቸውን ዳግም ህይወት እንዳንዘራባቸው ነው። ድክመታችን ህብረት ማጣት ነው ካልን በረጅሙ የህብረት ፍለጋ ሂደታችን ምን ጠንካራ ጎን ምን ደካማ ጎን ነበረን ብሎ ማጤኑ የግድ ይሆናል። ያለፈውን በሚገባ መመርመር አለብን። ያለፈውን ሁሉ ማውገዙ ስልጡን ፖለቲካ ነው የሚሉ መሐይሞች አሉ-- አጥፊዎች ናቸው ። የነበረንን ተምክሮ መርሳት ሳይሆን እንዲያውም አያውቁትም ። በመሆኑም የመመርመር ችሎታ የላቸውም ። ወያኔ እንዴት እንዴት አድርጎ ለድል በቃ? ማን አገዘው? ኢሕአዴግ ብሎ ሲያወናብድ ማን እሰየው ብሎ ተከተለው? ማን ሀገር ወዳድ ጸረ ወያኔ ሀይሎችን አወገዘ? ጦረኛ ብሎ ወነጀለ? ወያኔ በጎጥና በጎሳ ሲከፋፍል ማን ደግፎት ከጎኑ ተኮለኮለ? ማን? መመለስ ያለባቸው ጥያቄዎች ናቸው ። ለምላሽ ግን ማወቅን ይጠይቃል ። ያለፈውን የታገለውን ትውልድ በጅምላ የሚያወግዙ፤ ለአሜሪካ ርዕዮት ተጎንብሰው እያሉ ያንን ትውልድ የባዕድ ርዕዮት ተከትሎ ነበር ብሎ ማብጠልጠሉ የማይቀፋቸው ፤ ለሀገርና ለሕዝብ ሲል የተዋደቀውን ዜጋና ትውልድ ሊያወግዙ ሲነሱ የማያፍሩ ሁሉ ታሪክን የረሱ፤ ማወቅ መገንዘብ ያቃታቸው ከንቱዎች ናቸው ። ወያኔ አማራን ጠላት ብሎ ሲነሳ ማን በዚህ ወንጀሉ ደገፈው? ማን ሊሾም ተኮለኮለ? ማንስ ልጆቼ ብሎ ወያኔን አቆላመጠ? ማንስ የስልጣን ፍርፋሪ ተካፋይ ሆነ? ወያኔ ታጋዮችን ሊከፋፍል ሲነሳስ ማን ተባበረው? ማን አስመሳይ ተቃዋሚ ሆኖ ታጋዮችን በሰርጎገብነት አጠፋ፤ ጎዳ? ማንስ የሕዝብን የሙት ከተማ አድማ ከወያኔና ባዕዳን ጋር ሆኖ አደናቀፈ? ይህ ሁሉ ሲመለስ ፤ መልስ ሲገኝ ደም የተገበረበት ታሪክ ነው ። በ1997 ከ300 ዜጋ በላይ ተጨፍጭፎ ብዙ ሺው ደግሞ ለእስርና ስየል ተዳርጓል ። ማነው ተጠያቂ? ያስ ሁኔታ እንዳይደገም፤ ከሕዝብ ጎራ ነን ብለው እንዳያጠቁንና እንዳያስጠቁን ምን ማድረግ አለብን? ወይንስ አሁንም ወያኔ ድርጅትና ሰርጎገቦችን እየቀፈቀፈ ያውናብደናል? ይመታናል ? ምዕራቦቹ ለወያኔ ድል ምን አደረጉ? ዛሬ የህዝብን ትግል ለማፈን ምን እያደረጉ ናቸው ? ከእባብ ዕንቁላል ርግብ ይወለዳል ወይስ ወያኔ ሰማይ ከመሬት ቢገናኝ የማይለወጥ ጸረ ኢትዮጵያ ቡድን ነው ?

በቂና የሚያስተምር ታሪክ ተመክሮ አለን ። የ1997 ኡ ምርጫ ተመክሮ --ያውም ስንቱን ዜጋ ሕይወት ያሳጣ--አለ ። ታዲያ ዛሬ ያንኑ ስህተት ለመድገም ምን የሚያስሮጥ አለ? በወያኔ የምርጫ ህግና አስመራጭ ኮሚቴ ስር ተሰልፎ ልመረጥ ማለትን ምን አመጣው ? ምርጫ በወያኔ ባለፈው ለአንድ ተቃዋሚ ነው ለተባለ አባል የፓርላማ ተብየው አባልነትና ደሞዝ ስጥትቶታል --ሌላ የተገኘ ውጤት አልነበረም ። 20 ና 30 ቀርቶ መቶ ተቃዋሚ ነን ባዮች ቢመረጡም መሰረታዊ ለውጥ አይኖርም-- ፍጹም ስልጣን በወያኔና በጠመንጃው ላይ የምትመካና የምትቃኝ ናትና ። ነጋ ጠባ የሚሞኝን የሚያዝንለት ብዙ ሰው አይኖርም--ይበለው ወይም ይበላቸው ይሉታል እንጂ ። ትላንት ዕርቅ እናመጣለን ብለው የወያኔን ዕቅድ ያሟሉትን አጉል አውቅን ባዮችንስ እንደገና ተጨፍን አሞኙን ማለት ይገባናል ? የሙሰናዋ እቴጌ ገንዘብ የለኝም፤ ከምድረ በዳ አይጥ ባላነሰ ድሀ ነኝ ስትል ታዲያ ለምን አምነናት መዋጮ አንሰበስብላትም ? መጃጃል እስከመቼ? ከዚህ ሁሉ ለመዳን ታሪካችንን ማወቅና አለመርሳት ነው መፍትሔው። ባለፈው ሰሞን ማንዴላ ባረፈ ወቅት የእሱንም ሆነ የደቡብ አፍሪካን ታሪክ ጠንቅቀው የማያውቁና አፓርቴይድ ወድቆም ሳለ ገና ነው በሚል የትጥቅ ትግልን አማራጭ አንተውም መባሉን የማያውቁ ወይም የዘነጉ፤ እርቅና ሰላም ተብሎ ስንት ተሞክሮና ስንት ስቃይም ተቃዋሚዎች ተቀብለው (አዲስ አበባ የተጓዙ የኢዴሃቅ አባላት የደረሰባቸውን ያስታውሷል ) የተገኘውንም ተመክሮ ዘንግተው ዕርቅ ዕርቅ ብለው ሊሰብኩ የተነሱ ነበሩ። አለማወቅ፤

ሳያውቁም መካሪ ወቃሽ ሆኖ መነሳት--ግብዝነት ማለት ነው ። ይህን ጠባይና ዝንባሌ እያሳዩ ያሉትን ምሁር በሉን ባዮች ዜጎች ዛሬ በተቃዋሚው ጎራ ሆነ በሕዝብ ዘንድ የተናቁ ናቸው ።

ታሪኩን የረሳ ስህተቱን ይደግማል ። የሀገርን ህልውና በሚመለከት ወሳኝ ትግል ደግሞ ስህተት የሚፈቀድ ወይም በቀላሉ የሚታይ አይደለም ። ሀገርን ማጣት መቀማት ሊከተል ይችላልና ። ደግም ወያኔዎች የሕዝብ ትግል ላይ ጋሬጣ ሆነው ጉዳት አድርሰዋል። የተታለለላቸው ዜጋ ቁጥርም ቀላል አልነበረም ። በቃ ከአሁን ወዲያ። ጸረ ኢትዮጵያና ጸረ ሕዝብን አገዛዝ በመራራ ትግል ማስወገድ ብቻ ነው አማራጩ። ታሪክን ካልረሳን ይህን ነው የምንገነዘበው ።

ጸረ ወያኔው ትግላችን ይፋፋም !!